በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚ ችሎት

የሰ/መ/ቁጥር 223024

ጥቅምት 24 ቀን 2015 ዓ/ም

ዳኞች ፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካቾች ፡ 1ኛ.አቶ ለገሰ አብዲ

2ኛ. ወ/ሮ ሙሉ አያኖ

ተጠሪዎች ፡ 1ኛ. አቶ ኤፍሬም ወዳጆ

2ኛ. አቶ ተዘራ ተሰማ } ቀረቡ

መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው ተጠሪዎች በችሎቱ የተሰየሙ ዳኞች ከችሎት ይነሱልኝ በሚል ባቀረቡት አቤቱታ ላይ ብይን ለመስጠት እና የቅጣት አስተያየት ለመቀበል በመሆኑ የተጠሪዎችን አቤቱታ መርምረን ተከታዩን ብይን ሰጥተናል፡፡

## ብይን

ተጠሪዎች በጥቅምት 22 ቀን 2015 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ በችሎቱ የተሰየምነው ዳኞች በዚህ መዝገብ በጥቅምት 02 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጣችሁት ውሳኔ በሰበር አጣሪ የተያዘውን ጭብጥ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በመቀየር፤ ማስረጃ ለመመዘን ስልጣን ሳይኖራችሁ የአመልካቾችን ማስረጃ ብቻ በመመዘን እና በጉዳይ አስፈጻሚ በኩል አመልካቾች ገንዘብ ለችሎቱ ዳኞች በመስጠታቸው የተወሰነላቸው ስለሆነ ዳግም ዳኝነት እንዲታይልን ያቀረብነውን አቤቱታ በገለልተኛነት ልታዩልን አትችሉም፡፡ በመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 133/2013 አንቀጽ 34 መሰረት ከችሎቱ ልትነሱ ይገባል በሚል ነው፡፡ እንደሚታወቀዉ ዳኞች የሚቀርብላቸውን ክርክር የነፃነትና የገለልተኝነት መርሕን በመከተል የመወሰን ኃላፊነት አለባቸው፡፡ የዳኝነት ነጻነት በዓለም አቀፍ ሕግጋት፣ በኢ.ፊ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥትና በተለያዩ አገራዊ ሕግጋት እዉቅና የተሰጠዉና ጥበቃ የተደረገለት መርህ ነዉ፡፡ በተለይ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 78/1 እና 79(2 እና 3) ስር ስለፍርድ ቤቶች ተቋማዊ ነጻነት እና የዳኞች ግላዊ ነጻነት በተመለከተ እንደተደነገገዉ ፍርድ ቤቶች ከማንኛዉም የመንግሥት አካል፣ከማንኛዉም ባለሥልጣን ሆነ ከማንኛዉም ሌላ ተጽእኖ ነጻ እንደሆኑና ዳኞችም ከሕግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ ሳይመሩ የዳኝነት ተግባራቸዉን በሙሉ ነጻነት እንደሚያከናዉኑ ተደንግጓል፡፡ የገለልተኝነት መርሕ መሠረት ሀሳብም አንድ ዳኛ ወይም ችሎት ለተከራካሪዎች ያለው አመለካከት፣ የተከራካሪዎች የተለያዩ ግላዊ ምክንያቶችን ግምት ውስጥ ሳያስገባ እንዲሁም በጉዳዩ ወይም በተከራካሪዎች ላይ የተለየ ስሜትና ፍላጎት ሳይኖረው ተከራካሪዎችን ገለልተኛ በሆነ መንገድ ማስተናገድ እና ውሳኔ መስጠተን የሚመለከት ነው፡፡ ነፃና ገለልተኛ በሆነ የዳኝነት አካል መዳኘት የተከራካሪዎች ወይም የዜጎች መብት በመሆኑ ዳኞች ይሕን መሠረታዊ መርሕ የማክበር እና የማስከበር ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡ የፍርድ ቤቶች ገለልተኛት ፍርድ ቤቱ በእውን ገለልተኛ ሆኖ ጉዳዮችን መወሰኑን ብቻ ሳይሆን ጠቅላላ የፍርድ ሂደቱ ገለልተኛ መሆኑን ተከራካሪዎችና ጠቅላላ ሕዝብ እንዲረዳው የሚያደርግ የአሠራር ሥርዓት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ በኢፌዴሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 79(2) ፍርድ ቤቶች ከማናቸውም ተፅዕኖ ነጻ ናቸው የሚለው አገላለጽ ፍርድ ቤቶች ከውጭ ተፅዕኖ ብቻ ሳይሆን ከውስጣቸው በተለይም ዳኞች ከግል ፍላጎታቸውና ስሜታቸው ጭምር ነጻ ሆነው አንድን ጉዳይ በገለልተኝነት ማየትና ውሳኔ የመስጠት ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑን የሚያካትት ነው፡፡

ዳኛ ወይም ችሎት ጉዳዩን ገለልተኛ ሆኖ ያያል የሚለው የሕግ ግምት የሚወሰድበት ነው፡፡ ሆኖም ይሕ ግምት ተቃራኒ ማስረጃ ቀርቦ ዳኛው ወይም ችሎቱ ገለልተኛ አለመሆኑ ከተረጋገጠ ጉዳዩን ከማየት እንዲነሳ ወይም ችሎት እንዲቀየር የሚደረግበት አሠራር ዓለምአቀፍ ተቀባይነት ያለው አካሄድ ነው፡፡ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ 1234/2013 አንቀጽ 33 - 35 ላይ ዳኛን ከችሎት የሚያስነሱ ምክንያቶችና የሚነሳበት ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡ ሥርዓቱ መዘርጋቱ በአንድ በኩል ዳኛው ወይም ችሎቱ ጉዳዩን በገለልተኛት አያይም የሚለውን ወገን ችሎት እንዲቀየርለት ወይም ዳኛ ከችሎት እንዲነሳለት የመጠየቅ መብቱን በመፍቀድ የተከራካሪው ወገን ገለልተኛ በሆነ ዳኛ ወይም ችሎት የመዳኘት መብትን ማስከበር ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በማስረጃ ያልተደገፈ ምክንያት ወይም መረጃ በማቅረብ የፍርድ ሂደቱን ያላግባብ እንዳይጓተት፣ መሠረትቢስ በሆነ መረጃ መነሻነት በችሎት ወይም በዳኛው ስብዕና ላይ ጉዳት እንዳይደርስ በመከላከል የዳኛው የውሳኔ ነፃነት (decisional independence) ማስጠበቅ እና ተከራካሪዎች ከችሎት ይነሳልኝ አቤቱታ ሲያቀርቡ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ከታለመለት ዓላማ ውጭ ወጥቶ ዳኛ ወይም ችሎት የመምረጥ ሂደት ውስጥ እንዳይገቡ የመከላከል ዓላማ ያለው ነው፡፡

ተጠሪዎች የችሎቱ ዳኞች ገለልተኛ አይደላችሁም የሚሉበት አንዱ ምክንያት በሰበር አጣሪ የተያዘውን ጭብጥ በመቀየር ውሳኔ ሰጥታችኋል በሚል ነው፡፡ አመልካቾች ባቀረቡት የሠበር አቤቱታ መነሻነት ጉዳዩ በሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል በመባሉ ለተጠሪዎች የሰበር አጣሪ ችሎቱ የያዘው ጭብጥ እና የአመልካቾች የሠበር አቤቱታ ማመልከቻ እንዲደርሳቸው ተደርጓል፡፡ የሠበር ችሎት በዋነኛነት የሚመራበት የተለየ የሥነ-ሥርዓት እስከሌለ ድረስ ሰበር ችሎቱ ሊመራ የሚችለው በፍትሕ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ እንደነገሩ ሁኔታ ለቀጥታ ክስ እና ስለይግባኝ ክርክር አመራር የተዘረጋውን ሥነ-ሥርዓት በመከተል ነው፡፡ እንደዚሁም በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 27 ላይ ስለሰበር አቤቱታ አቀራረብ የተመለከተ ሲሆን የሠበር አቤቱታው በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ ያስቀርባል የሚባል ከሆነ ደግሞ ያስቀርባል የተባለበት ነጥብ ከሠበር ቅሬታው ጋር ለተጠሪ ደርሶ ተጠሪ መልሱን እንደሚያቀርብ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 28/3 እና 4 ተመልክቷል፡፡ በዚህም መሰረት የአመልካቾች የሠበር ቅሬታ ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ ጋር ለተጠሪዎች ተልኮ ተጠሪዎችም መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡

በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 የሠበር ችሎቱ የግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተጠናቆ መዝገቡን ሲመረምር በሠበር አጣሪ ችሎት የተያዘውን ጭብጥ ቀይሮ ውሳኔ መስጠት የሚችል ስለመሆን አለመሆኑ የተመለከተ ነገር የለም፡፡ በቀጥታ ክስ የክርክር ሂደት ፍርድ ቤቱ የያዛቸውን ጭብጦች ለውጦ ውሳኔ መስጠት እንደሚችል በፍ/ሥ/ሥ/ሕጉ በአንቀጽ 251እና342 ላይ ተመልክቷል፡፡ ይህ ድንጋጌ በተመሳሳይ መልኩ(analogy) በሠበር ክርክር ወቅትም ተፈጻሚ ሊሆን ይገባል፡፡ እንደዚሁም የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 328(2)(3) አቀራረጽ የይግባኝ አቤቱታ አቅራቢው ባቀረበው የቅሬታ ዝርዝር ፍርድ ቤቱ በዋናነት መወሰን እንዳለበት የሚያዝ ሲሆን በይግባኝ አቤቱታው ከተመለከተው ዝርዝር ክርክር ወጥቶ ሊወስን የሚችለው በንዑስ ቁጥር ሦስት እንደተመለከተው ፍርድ ቤቱ ጭብጥ አድርጎ በያዘው እና ግራቀኙ እንዲከራከሩበት እድል በተሠጠበት ጉዳይ ላይ ብቻ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ በዚህም መሰረት ተጠሪዎች አመልካች ባቀረቡት የሠበር አቤቱታ ክርክር እና ፍርድ ቤቱ የያዘው ጭብጥ ከመጥሪያ ጋር የተላከላቸውም ፍርድ ቤቱ መሠረት አድርጎ ሊወስንበት የሚችለው በሠበር አቤቱታው በተመለከተው ወይም/እና የሠበር አጣሪ ችሎት በያዘው ጭብጥ ላይ ሊሆን ስለሚችል ተጠሪዎች የመደመጥ መብታቸው በተሟላ ሁኔታ የሚከበረው ሁሉቱም ሲደርሳቸው መለስ ሲሰጡ መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ በተጨማሪም የሠበር ችሎት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በሠበር አጣሪ ችሎት የተያዘውን ጭብጥ መቀየር እንደሚችል፤ ተጠሪም መልስ ማቅረብ ያለበት ያስቀርባል በተባለው ጭብጥ ላይ ብቻ ሳይሆን የሠበር ቅሬታውን መሰረት በማድረግ መሆን እንዳለበት እና ተጠሪ በጭብጥነት በተያዘው ነጥብ ላይ ብቻ መልስ የሚሰጥ ከሆነ በሌሎች በሠበር ቅሬታ ላይ በተመለከቱ ነገሮች መልስ ማቅረብ እንዳልፈለገ ተቆጥሮ በተቀየረው ጭብጥ መሰረት ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሠበር መዝገብ ቁጥር 169554 እና በሌሎች መዝገቦች የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ ነው፡፡

በመሆኑም ተጠሪዎች በሠበር አቤቱታው ላይ ሆነ የሠበር አጣሪ ችሎት በያዘው ጭብጥ ላይ መልስ የማቅረብ መብታቸው ተከብሮ እያለ መብታቸውን በሙሉ ሳይጠቀሙ የሠበር አጣሪ ችሎት በያዘው ጭብጥ ላይ ብቻ መልስ አቅርበዋል ቢባል እንኳን በቀሪው ጉዳይ መልስ የማቅረብ መብታቸውን እንደተውት የሚያስቆጥር ከሚሆን በቀር ይህ ችሎት ጭብጥ ቀይሮ ውሳኔ ሰጥቶ እንኳን ቢሆን የሥነ-ሥርአት ግድፈት በመፈጸም የተጠሪዎችን የመሰማት መብት አጣቧል የሚያስብል እና የችሎቱ ገለልተኛነት ላይ ጥያቄ ሊፈጥር የሚችል አይሆንም፡፡

ሌላው ተጠሪዎች በችሎቱ የተሰየሙት ዳኞች ከችሎቱ ሊነሱ ይገባል የሚሉበት ምክንያት ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ሳይኖራችሁ የአመልካቾችን ማስረጃ ብቻ በመመዘን የፍሬ ነገር ድምዳሜ ቀይራችኋል የሚል ነው፡፡ እንደሚታወቀው ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 80/3/ሀ እና በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 የተሰጠው የዳኝነት ስልጣን መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸውን የመጨረሻ ውሳኔዎች ማረም ነው፡፡ በዚህ ሥልጣኑ ተከራካሪ ወገኖች ማስረጃ ለመቀበል፣ ለመስማትና ለመመዘን ሥልጣን ለተሰጣቸዉ የስር ፍርድ ቤቶች ያቀረቡትን ማስረጃዎች የመመዘን ጉዳይ ዉስጥ በመግባት ማስረጃዎችን በመመርመርና በመመዘን አከራካሪ የሆነዉ የፍሬ ነገር ጭብጥ መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥልጣን ሰበር ችሎቱ አልተሰጠዉም ማለት ነው፡፡ ሆኖም የማስረጃ አቀራረብን፣ አግባብነትን፣ ተቀባይነትን እና ማስረጃ አቅርቦ አንድን ፍሬ ነገር የማስረዳት ሸክም መርህ (Production, relevancy, admissibility and burden of proof of evidence)እንዲሁም የማስረጃ ምዘናን ወይም የማስረዳት ደረጃን (standard of proof or weight of evidence) የሚመለከቱ መሰረታዊ መርሆዎች ተጥሶ የተሰጠ የመጨረሻ ዉሳኔ ሲኖር መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሚሆን በሰበር ሰሚ ችሎት የሚታረም ይሆናል፡፡ በዚህ መዝገብ በጥቅምት 02 ቀን 2015 ዓ.ም በተሰጠው ውሳኔ ላይም በስር ፍርድ ቤቶች የማስረጃ ምዘና መርህ ጥሰት ተፈጽሟል በሚል በስር ፍርድ ቤት በግራ ቀኙ በማስረጃነት ለቀረቡ ሰነዶች ተገቢው ዋጋ ሳይሰጥ የማስረጃ ምዘና መርህ ጥሰት የተፈጸመ በመሆኑ ይህንኑ በማረም የሰጠነው ውሳኔ ነው፡፡ እንደዚሁም ውሳኔው የማስረጃ ምዘና መርህን በተመለከተ የተፈጸመውን ስህተት የሚያርም ብቻ ሳይሆን የንግድ መድብል ሊባል የማይችል ባዶ ቦታ በንግድ መደብር ስም በሽያጭ ለማስተላለፍ የተደረገው ውል ህገ ወጥ በመሆኑ በፍርድ ቤት ህጋዊ ውጤት ሊሰጠው አይገባም በሚል የተሰጠ ውሳኔ ነው፡፡ በመሆኑም የሰጠነው ውሳኔ በስር ፍርድ ቤቶች መሰረታዊ የማስረጃ ምዘና መርህ ጥሰት ተፈጽሟል እና ሕጉም ሕጋዊ ዉጤት የለዉም በሚል እምነት የስር ፍርድ ቤቶችን ስህተት ማረማችንን ከሚያሳይ በስተቀር ተጠሪዎች እንደሚሉት ከስልጣናችን ውጪ በመውጣት እንደገና ማስረጃ መዘናችኋላ የሚያስብል አይደለም፡፡

በመጨረሻም ተጠሪዎች ውሳኔው የተሰጠው አመልካቾች በጉዳይ አስፈጻሚ በኩል ለዳኞች ገንዘብ በመስጠቱ ነው የሚል እምነት አለን በሚል ያቀረቡትን ምክንያት ስንመለከት እንደሚታወቀው በአንድ ክርክር ላይ ተሳታፊ የሚሆኑት ሁለት ተከራካሪ ወገኖች ናቸው፡፡ በዚህም ምክንያት አንደኛው ተከራካሪ ወገን ይፈረድለታል ሌላኛው ተከራካሪ ወገን ደግሞ ይፈረድበታል፡፡ ይህ የፍርድ ቤት የስራ ባህሪ ነው፡፡ ፍርድ ቤትም አንዱን ወገን የክርክሩ ረቺ በማድረግ ለመወሰን የግራ ቀኝ ተከራካሪ ወገኖችን ክርክር ከሕግ እና

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ከማስረጃ አንጻር ብቻ መርምሮ ውሳኔ የመስጠት ኃላፊነት ያለበት መሆኑ ግልጽ ነው። ነገር ግን አንድ ዳኛ አንድን ወገን ተጠቃሚ የሚያደርግ ውሳኔ የሰጠው ከባለጉዳዩ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ገንዘብ በመቀበል ከሆነ ዳኛው ይህንን ማድረጉን የሚያሳይ ማስረጃ ሊቀርብበት ይገባል። ዳኛው ድርጊቱን መፈጸሙ ከተረጋገጠም በሕግ ተጠያቂ ሊሆን ይገባል። በተያዘው ጉዳይ ተጠሪዎች በችሎቱ የተሰየሙት ዳኞች ውሳኔ የሰጡት በገንዘብ መሆኑን በወሬ ደረጃ ሰምተናል ከማለት ባለፈ ከአቤቱታቸው ጋር አያይዘው ያቀረቡት ማስረጃ የለም። አመልካቾች ፍርዱ ከመሰጠቱ በፊት እንዲህ አይነት ወሬ ከሰሙ ለምን ለችሎቱ ወይም ለሌላ ለሚመለከተው አካ በማሳወቅ ፍትህን የማገዝ ኃላፊነታቸውን አልተወጡም? የችሎቱ ዳኞች ውሳኔውን የሰጠነው ተጠሪዎች በወሬ ሰማን እንደሚሉት ከአመልካቾች ወይም ከጉዳይ አስፈጻሚ ገንዘብ ተቀብለን ሳይሆን ሕግን እና ማስረጃን መሰረት አድርገን ተገቢ ነው ብለን ያመንበትን በመሆኑ ተጠሪዎች በዚህ ረገድ ያቀረቡት ምክንያትም ከችሎት የሚያስነሳ ሆኖ አላገኘነውም። በአጠቃላይ ተጠሪዎች የዳግም ዳኝነት አቤቱታ እንዳንመለከት የችሎቱ ዳኞች ከችሎት እንድንነሳ ያቀረቡት አቤቱታ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 33 ስር የተዘረዘሩትን ምክንያቶች መሰረት በማድረግ የቀረበ ባለመሆኑ ተጠሪዎች ያቀረቡትን ዳኞች ከችሎት ይነሱልን አቤቱታ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 34/3 መሰረት አልተቀበልነውም።

ከተባለ በኋላ ተጠሪዎች በጥቅምት 23 ቀን 2015 በዋለው ችሎት በችሎት መድፈር ጥፋተኛ ተብለው የጥፋተኝነት ውሳኔ የተሰጠባቸው በመሆኑ የቅጣት ማቅለያ አስተያየት እንዲያቀርቡ ተጠይቀው

1ኛ አመልካች (ተጠሪ በጹሁፍም በቃለም ለችሎት እና ለዳኞች ክብር በማይመጥን መልክ በመናገሬ እና የችሎቱን ክብር  በመድፈሬ ይቅርታ እጠይቃለሁ፡

የቅጣት አስተያየት በጹሁፍ አላቀረብንም በቃል እናስመዘግባለን በማለት

1ኛ ተጠሪ አይምሮዬ በታወከበት ሁኔታ ነዉ ድሪጊቱን የፈፀምኩት አይምሮዬ  የታወከበት ምክንያትም በይዞታዉ ላይ ለ13 ዓመት ስሰራበት ቆይቼ 5 ጊዜ ፍ/ቤት ተሟግቼ ነዉ  ቦታዉን ለማግኘት  በርካታ መሰዋትነት ከፍያለሁ በዚህ ምክንያት በስሜት የተናገርኩት  ነው

2ኛ የቤተሰብ አስተዳዳሪ ነኝ በማስረጃነትም የልጆች የክርስትና ወረቀት አቅርቤአለሁ

3ኛ በጥፋቱ መፀፀቴን

4ኛ ከዚህ በፊት ጥፋተኛ አልተባልኩል የዘወትር ፀባዬም መልካም ነው

5ኛ በአጠቃላይ ጥፋት ያጠፋሁ ቢሆንም እራሴን መቆጣጠር ባለመቻሌ የተፈፀመ ጥፋት ስለሆነ በማስጠንቀቂያ እና በተግሳጽ እንዲያልፈኝ ካልሆነም በገንዘብ መቀጮ እንዲያልፈኝ የእስርም ቅጣት ከሆነ ሰርቼ የምተዳደርበት ጉዳይ /ስራ/ ተቋርጦ የልጆቼ ገቢ ስለሚቋረጥ እስራቱ በገደብ እንዲደረግልኝ እጠይቃለሁ ብለዋል።

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

2ኛ ተጠሪ፡- በችሎት ቀርቤ አሳቅም የቤተሰብ አስተዳዳሪ ነኝ ብዚ ቤተሰቦች ባለው ሀገራዊ ችግር ከሀገር ቤት መተው እኔ ጋር የሚኖሩ እና እናቴንም እያስታመምኩ እገኛለሁ

- ከዚህ በፊት የወንጀል ጥፋት ፈፅሜ አሳቅም መልካም ስነ ምግባር ያለኝ ነኝ ስለዚህ ቅጣቱ በገንዘብ ተደርጐ እንዲወሰንልኝ እጠይቃለሁ ለፈፀምኩት ድርጊትም ይቅርታ እጠይቃለሁ ብለዋል፡፡
- የምተዳዳረው የመኪና ማቆሚያ እና ማሳደሪያውን በማከራየት ነው ብለዋል፡፡

## ቅጣት

- ተጠሪዎች ጥፋተኛ የተባሉት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 449/1 በመተለፍ ሲሆን ይህን ድንጋጌ መተላለፍ ከአንድ አመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም እስከ ሶስት ሺ ብር መቀጮ እንደሚያስቀጣ ተደንግጓል፡፡
- ተጠሪዎች ያቀረቡትን የቅጣት ማቅለያ ከግምት በማስገባት እንዲሁም 1ኛ ተጠሪ የሕግ አማካሪ /ጠበቃ/ ሆነው ይህንን ድርጊት መፈፀማቸው ጥፋቱን የሚያከብደው በመሆኑ በቀላል የእስራት ቅጣት ሊቀጣ ይገባል ብለናል የቅጣቱ መጠንም 1ኛ ተጠሪን ያርማል እንዲሁም ሌሎችን ያስተምራል ባልነው የ 6 ወር/ ስድስት ወር/ ቀላይ እስራት ሊቀጡ ይገባል ብለናል፡፡
- የቅጣቱን አፈፃፀም በተመለከተ 1ኛ ተጠሪ የሕግ አማካሪ/ጠበቃ/ በመሆናቸው እስራቱ ተፈፃሚ ቢደረግ የደንበኞቻቸው ጉዳይ ላይ ተፅእኖ ይፈጥራል በሚል እምነትና በጥፋቱ መፀፀታቸውን እና መታረማቸውን የገለፀ በመሆኑ በወ/ሕ/ቁ 192 መሰረት እስከ 2 ዓመት ተገድቧል፡፡
- 2ኛ ተጠሪም በድርጊቱ መፀፀታቸውን እና ባለማወቅ የፈፀሙት ድርጊት መሆኑን የገለፀ በመሆኑ በተግሳጽ እና በምክር ሊታለፍ ይገባል ብለናል፡፡

## ትእዛዝ

- 1ኛ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 34/3 መሰረት የችሎት ዳኞች ከችሎት ልንነሳ አይገባም በሚል በተሰጠው ትእዛዝ ላይ ሌላ ችሉት እንዲወስን መዝገቡ በሬጅስትራር ፅ/ቤት በኩል ይተላለፍ፡፡
- 2ኛ ተጠሪዎች በጥቅምት 22 ቀን 2015 በተፃፈ ዳኞች ከችሎት እንዲነሱ በሚጠይቅ አቤቱታ የችሉቱ ዳኞች በጉዳዩ አስፈፃሚ በኩል በስር አመልካች ልጅ የኂላእሸት ለገሰ ከችሎቱ ሁለት ዳኞችን አናግረው ገንዘብ መስጠታቸው የኂላ እሸት ለገሰ ወንድም የሆኑት ብዙነህ ለገሰ እና ሲሳይ ለገሰ የተባሉት ሲያወሩ ዳዊት የተባሉ የሕግ ባለሙያ የ1ኛ ተጠሪ ጓደኛ መስማታቸውን እና ለ1ኛ ተጠሪ መንገራቸውን፣ 2ኛ ተጠሪ ደግሞ የአካባቢው ሰው ሁሉ አመልካቾች ለዳኞች ገንዘብ መስጠታቸውን ሲያወሩ መስማታቸውን ለችሎቱ የገለፁ በመሆኑ ተጣርቶ እውነታው እዲታወቅ ተጠሪዎች የችሎቱ ዳኞች እዲነሱ በማለት በጥቅምት 22ቀን 2015

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

ዓም ጽፈው ያቀረቡት አቤቱታ ከዚህ ትእዛዝ ጋር ለዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የስነምግባር ጥሰት ጥቆማ እና(የሙስና ተግባራት ጥቆማ ተቀባይ ክፍል) ይተላለፍ ብለናል፡፡

- 3ኛ ለተጠሪዎች መፈቻይፃፍ፡፡

አ/መ
የማይነበብ የአምስት ዳኞች
ፊርማ አለበ